«እንኳን ለብርሃነ ትንሣኤው በሰላም አደረሳችሁ»

ፕሬስ የሕዝብ ዘብ ነው

# ጦቢያ

ጦቢያ 12ኛ ዓመት ቁጥር 9 ሚያዝያ 22 1997




## ዶ/ር ነገደ ጎበዜ እንዲህ ይላሉ

ልዩ ቃለ- ምልልስ

✉ 22373 ☎ 23-26-04
ፋክስ:- 251-1-23-26-05
E-mail Address.
akpac @telecom.net.et
የባንክ ሂሳብ ቁጥር 3167
የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣
አዲስ አበባ ቅርንጫፍ፣ አዲስ አበባ

**ዋና ሥራ አስኪያጅ**
ግርማ ፈይሣ
09/20-76-21

**ዋና አዘጋጅ**
አረጋ ወልደቂርቆስ

**ም/ዋና አዘጋጅ**
አጥናፉ ዓለማየሁ

**ሪፖርተሮች**
ሁሴን ከድር
መሰንበት ኃይሉ

**ኮምፒዩተር ቅንብር**
አረጋሽ ፀጋዬ

**ኮምፒዩተር ጽሁፍ**
አዲስዓለም ደምሴ
ሲያባራ ወልዴ

**ማስታወቂያ፣ ሽያጭና ሥርጭት**
ሙሉጌታ ወ/ሚካኤል
09/67-09-91
ዳንኤል ወርቅነህ

የፊት ገጽ ሽፋን ዲዛይን (አከፓክ)

**አሳታሚ**
አጥቢያ ኮከብ የኅትመትና የማስታወቂያ ሥራ
ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር
**አከፓክ**

«ጦቢያ» መጽሔት ከሚያዝያ 1984 ጀምሮ በየወሩ የሚታተም፣
በአጠቃላይ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር መጽሔት ነው::
መጽሔቱ ከማናቸውም የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር ያልወገነና የግለሰቦችን
ነጻ አስተያየት የሚያስተናብር ነው::

አሥራ ሁለተኛ ዓመት፣ ቁጥር 9፣ ሚያዝያ 22 1997

## ኢትዮጵያን ወደ ትክክለኛ ሀዲድ ለመመለስ

«...እነዚህን በጥቂቱ ተጨልልፈው የቀረቡትን ችግሮች ለመፍታት ምንድነው መደረግ ያለበት? የማነውስ ኃላፊነት? የኢትዮጵያዊያንን ችግር የሚያውቅና የሚፈታ ኢትዮጵያዊ ማነው? የሚሉትን ጥያቄዎች በምርጫ አፋፍ ላይ ቆመን ከምናነሳቸው ዐበይት ጥያቄዎች መካከል ዋናዎቹ ይመስሉኛል»

ዳንዴው ሠርቤሎ ገጽ 4

## የኦሮሞ ጉዳይ... ወደዬት፣ ወደዬት?

«...ቀሪው ኢትዮጵያዊ ፍላጎቱ የሚረካውና ልቡ የሚረጋው፣ አነግ ልክ እንደእነዚህ ሁለቱ የኦሮሞ ድርጅቶች የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት በቅድሚያ ይጠበቅለት የምትለዋን ጥያቄ ከፕሮግራሙ ሰርዞ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት መቆሙን በማያወላውል አኳኋን ሲያረጋግጥ ነው:: ለውጥ የለም ባዮችም ዋና መከራከሪያ ነጥባቸው ይኸው ጉዳይ ነው::»

ሐሰን ዑመር አብደላ ገጽ 11

## ኡኡታ አለኝ ለአገር መጥኝ!

«...እኛ ኢትዮጵያውያን፣ እንደዓለም ሕዝቦች ሁሉ የሰው ዘር ልጆች ነን ብለን ከተነሳን ግን፣ ዓይናችንን፣ ወኔአችንን፣ አእምሮአችንን፣ መንፈሳችንንና ሕሊናችንን ከወያኔ ላይ፣ ለአንዲት ደቂቃም እንኳን ማንሳት የለብንም::»

ክቡር ሎሬት ብላቴን ጌታ ፀጋዬ ገ/መድኅን ገጽ 22

## ቃለ መጠይቅ

«...በዚህ መጽሐፍ ሳቢያ በኢሕአዴግ መሪዎች አካባቢ የተያዘውን ከብርክ የሚዋሰን ፕሮ ፓጋንዳ ስታዘብ ያኔ «ከባሩድ ይልቅ ብዕር የሚያስበረግገው ኃይል» ብለን የተቸነው ትዝ አለኝ:: «በማያውቅበትና ግራ በሚጋባበት» ሰላማዊ የትግል ስልት መፋለም የሚለው መስመር ምን ያህል ትክክለኛ እንደሆነ ከዚያን ጊዜ ይበልጥ ዛሬ ለመረዳት ችያለሁ:: ...ከዶክተር ነገደ መጽሐፍ ተብሎ የተጠቀሰው ከአቶ በረከት ጭንቅላት እንጂ ከእኔ መጽሐፍ የተወሰደ አይደለም:: አሳፋሪ ቅጥፈት ተጨምሮበታል::»

ዶክተር ነገደ ጎበዜ ገጽ 7

## ልዩ ጥንቅር

«... እንደዜጋ ሁኔታዎችን ሳጤን ካለፉት ዓመታት በጣም የተሻለ የተወዳዳሪ ፓርቲዎች ኃይል የሚታይበት ይሆናል ብዬ እገምታለሁ:: በጥቅል ግን ይኼ ፓርቲ አሸንፎ ሥልጣን ይይዛል ለማለት ያስቸግረኛል:: በአንድ ነገር ግን እርግጠኛ ነኝ:: ፓርላማው እንዳለፈው አንድ ሃሳብ ቀርቦ እጅ የሚወጣበት ፓርላማ ከመሆን የሚድን ይመስለኛል::

ተ/ፕሮፌሰር አያሌው ገጽ 16

## ተመልካች

«... ተማሪው በፈተና ወደቅሁኝ ከማለት ፋንታ መምህሩ ጣለኝ ካለ፣ መምህሩም የሚያዳላ ከሆነ፣ የተማሪ አመዳደቡ፣ ለተማሪዎች የሚቀርቡ መሣሪያዎችና አገልግሎቶች ወገናዊነትንና ጎጣዊነትን የሚያንፀባርቁ ከሆነ፣ የመምህራን ቅጥር፣ አመዳደብ፣ ዕድገት፣ የትምህርት ዕድል ማግኘት የብሔር ማንነትን የሚከተል ከሆነ የትምህርት ሥርዓቱ በስብሷል ወይም ፈርሷል ማለት ይቻላል::»

ወገኔ ገረሱ ገጽ 33

ሌሎች

◆ ከመልዕክት ሣጥናችን 2፣ ◆ ከአዘጋጁ ቢሮ 3 ◆ ልዩ ጥንቅር 16 ◆ የቋንቋ ቃና 19
◆ የመነጋገሪያ መድረክ 14 ◆ ሕይወታችንን እንታደጋት 20 ◆ ሙሸዘር 25
◆ ማኅበራዊ ኪን 26 ◆ ምርጫ 97 29 ◆ ማኅበረሰብ 35 ◆ ቅኝት 37

ሳተፍ መጋበዛቸው በምሳሌነት ሊጠቀስ የሚገባ ነው:: አሁንም እርምጃው እንደ መልካም የበጎ ፈቃድነት ምልክት ሊወሰድ የሚችል አብነት ነው::

ይህንን ጽሑፍ እናጠቃልል መሰለኝ:: ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የኦሮሞን ሕዝብ ትግል እንመራለን በሚሉት ድርጅቶች በጥቅል በኦ.ነ.ግ. አመራር በኩል በተለይ የምንመለከታቸው ከኦሮሚያ ሪፑብሊክ ምስረታ በመለስ ሊታዩ የሚችሉ የአቀራረብ ፍንጮችን በሰፊው ተመልክተናል:: የሌላውንም ኢትዮጵያዊ ምኞትና ስጋት ገረፍ ገረፍ አድርገን ለመመልከት ሞክረናል:: በአጭሩ ዕድገቶቹ ተስፋ አለምላሚ ናቸው ቢባሉ ብዙ ማጋነን የለበትም:: የትግሉ መጠንጠኛ የራስን ዕድል በራስ ከመወሰንና ነፃ ኦሮሚያ ሪፑብሊክን ከመመሥረት ይልቅ ወደ ብሔራዊ መብትና በፌዴራሉ ሥርዓት አማካኝነት የተገኙት ድሎች ከእጅ እንዳይነጠቁ ወደሚደረገው ትግል የተዟዟረ ይመስላል:: በዚህ ትግል ላይ ኦ.ነ.ግ. ብዙ አጋሮችን ያፈራል፣ ከጐኑ ያሰልፋል:: ለችግሮቻችን ሁነኛ መፍትሔ የሚሆን ቀመር ማግኘት አያዳግትም:: ስለዚህ ጉዳይ ኦ.ነ.ግ. መደራደር ያለበት ከገዢው ፓርቲ ጋር ሳይሆን መወያየት ያለበት ከመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ነው::

አሁንም ትንሽ ወደኋላ ተመልሼ ከሰባት ዓመት ገደማ በፊት «የኦሮሞ ጉዳይ... ከታሪክ ሰንበሮች ባሻገር» በተሰኘው ጽሑፍ ውስጥ የኦሮሞን የነፃነት ትግል ዚያድባሬና ኢሳይያስ አፈወርቂ የኢትዮጵያ ማጥቂያ መሣሪያ እያደረጉ መጠቀማቸውን በሰፊው ታትቶአል:: ይህ ደግሞ የኦ.ነ.ግ.ን ስም የማጥፋትና የማጥቆር ዘመቻ አይደለም:: አንዱ አምባገነን ቢሞትም ሌላው ዛሬም ነገ ተነገ ወዲያ በወያኔ ኢትዮጵያ ላይ ሌላ የጦርነት ዙር ሊያውጅበት በሚችል ሁኔታ ላይ ይገኛል:: የዛሬ ሰባት ዓመት ኦ.ነ.ግ. ፀረ-ወያኔ ትግሉን ከሻዕቢያ ጋር ተባብሮ በኢትዮጵያ ላይ የሚከፍተው ዘመቻ ውጤቱ ካለፈው የተለየ አይሆንም ብሎ አፍ ሞልቶ መናገር ነቢይነትን አይጠይቅም:: ሌላም ጠንቅ አለው:: ከላይ የተመለከትናቸው የመቀራረብ፣ የመነጋገር፣ የመተባበርና ትግሉን የማቀናጀት ተስፋዎች መና ሆነው ይቀራሉ:: ከላይ ስሙ የተጠቀሰው አቶ ሌንጮ ባቲ በተባለው ቃለ-መጠይቅ ላይ ኦ.ነ.ግ. ከኤርትራ ጋር የሚተባበረው ነገ ኤርትራዊያንን ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ለማቀራረብ ነው የምትለው መከራከሪያ ነጥብ የማሳመን ኃይል የላትም:: ልክ ከተቃዋሚዎች ጋር ያልተባበርነው ለእነሱ ፈርተን ነው መባሉ ተአማኒነት እንደሌለው:: የኢትዮጵያ ሕዝብ የኦ.ነ.ግ. ሦስተኛ ጉባኤ በኦሮሚያ ነፃ መሬት ላይ እንዳልተካሄደ በሚገባ ያውቃል:: ከአሥመራ ደግሞ ብዙ ለኢትዮጵያ የሚበጅ ነገር አይጠበቅም::

ያለጥርጥር ኦ.ነ.ግ. በሦስተኛ ጉባኤው ውሳኔዎች መግቢያ ላይ በትክክል እንዳስቀመጠው «የኦሮሞ ጥያቄ በአፍሪካ ቀንድም ሆነ በኢትዮጵያ ከሁሉ ጥያቄዎች አንገብጋቢና ማዕከላዊ ጥያቄ» እየሆነ መጥቷል:: የአካባቢያችንን ብቻ ሳይሆን ዓለም አቀፍ ሁኔታዎችን ጭምር ገምግመው የሕዝቡን ትግል ትክክለኛ ፈር የሚያሲይዙ መሪዎች እያስፈለጉ ናቸው:: ፈረንጆቹ እንደሚሉት «sense of history» ያላቸው:: እነ ዲጎል፣ እነ ቸርችል፣ እነ ቢስማርክ፣ እነ ማኦ ታላላቅ መሪዎች የተሰኙ ይህንኑ የታሪክ ነገረኛ የአቅጣጫ መቀየስ የአመራር ተሰጥኦ ነበራቸው:: ኢትዮጵያ ዛሬ እንደዚህ ዓይነቱ መሪ ያስፈልጋታል:: ከኦሮሞ አብራክ ከተገኘ ደግሞ ክርስትያኖች እንደሚሉት «በሰንበት ላይ በዓለ ማርያም» ነው:: ይህ ደግሞ ሽንገላ አይደለም::

## «ሸሳፋሪ...

ከገጽ 10 የዞረ

ነው:: ሁለተኛ ነገር ሕገ መንግሥት ሲሻሻል አገር ቢፈርስ ኖሮ አሜሪካ እስካሁን ቢያንስ ሃያ ጊዜ ፈርሳ ነበር:: ሶስተኛና ዋናው ቁም ነገር ግን ይኼ ሳይሆን ሌላ ነው:: «ከሞተች ሚስቴ ምን አለኝ ከአማቴ» ብለው፣ እኛ ሥልጣን ላይ ካልሆንን ይቺ አገር ምናችን ነች ብለው ቢሸነፉ በአመጽ ለመሠማራትና ቢሳካላቸው ኢትዮጵያን ለማተራመስ ሴራ እየጠነሰሱ ያሉት እነሱ ናቸው:: የኢሕአዴግ መሪዎች እንኳን ሕገ መንግሥታቸው ተቀይሮ «አንዲት ጊዜ እንኳን በምርጫ ከተሸነፍን ትልቅ ችግር ያጋጥመናል:: ኢትዮጵያ የማያባራ የትርምስ ወቅት ውስጥ ገብታ እንደ አገር የመቀጠሏ ነገር ያበቃላታል» ብለው በጽሁፍ ያሰቀመጡ ሰዎች ናቸው:: ይህንን በሰኔ ወር 1985 ዓ.ም በምስጢር በድርጅታቸው ውስጥ ያሠራጩትን ሰነድ Ethiopian Register የተባለው መጽሔት June 1996 እትሙ ይፋ ያደረገው ስለሆነ በእውነቱ ለዚች አገር እጨነቃለሁ የሚል ሁሉ ሊያነበው ይገባል ባይ ነኝ:: ባጭሩ «እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል» በሚለው የአህያዋ ፍልስፍና ተሰማርተው በአገራችን ሕልውና ላይ የሚያሴሩት የኢሕአዴግ መሪዎች ናቸው::

የመኢሶንም ሆነ የሕብረቱ እንዲሁም የሌሎች ዴሞክራቶችና አገር ወዳዶች ጭንቀት ይህንን የኢሕአዴግን «ወይ ተረግጣችሁ ተገዙ ወይ ደግሞ አገራቱን እበታትናታለሁ» የሚል ሤራ ለማክሸፍ ነው:: ዛሬ በሥልጣን ላይ ያለው ኃይል «ተራ» (ኖርማል) መንግሥት አይደለም:: ነገ በምርጫ ቢሸነፍ ደግሞ «ተራ» ተቃዋሚ ኃይል አይሆንም:: በርካታ የአገራችን ዴሞክራቶች ዘንድ ይህ ያለንበት አሳሳቢ ሁኔታ በቂ ግንዛቤ ያገኘ አይመስለኝም:: አንዳንዶቹ ልክ አገራችን መድበለ ፓርቲ ሥርዓት ውስጥ እንዳለች መስሏቸው ወይም ሆን ብለው እያስመሰሉ በነገው ምርጫ የተቻለውን ያህል መቀመጫ ለማግኘት፣ በቀጣዩ ደግሞ ይህንን ለማሻሻል እያሉ በመራኮት ላይ ይታያሉ:: በኔ ግምት ትግላችን በ51% አብላጭ መቀመጫ ኢሕአዴግን አሸንፎ ሥልጣን ከመያዝ በጣም እጅግ በጣም አልፎ የሚሄድ አገራዊና ሕዝባዊ ራዕይ ያነገበ ትግል መሆን አለበት:: የምንታገለው አንደኛ ለማሸነፍ፣ ሁለተኛ ደግሞ ከዚያው እኩል ኢሕአዴግ ከሸንፈቱ በኋላ ይህንን ሽንፈትና በምንታገልለት ዴሞክራሲያዊ ሁኔታ ለመፍጠር መሆን ይገባዋል:: የማያወላዳ የፖለቲካ የበላይነት የሚያስጨብጠን የተባበረ፣ አገራዊ ራዕይ ያለው ሰላማዊና ሕዝባዊ የትግል ማዕበል ለመቀስቀስ መሥራት አለብን የምለው ለዚህ ነው::

የሺህ ታጣቂዎች የትጥቅ ትግል «ማዕበል» አይደለም:: በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች በአንድነትና ለአንድ አላማ የሚንቀሳቀሱበት ትግል ግን ማዕበል ነው:: ባሳለፈው ሕዝባዊ ኃይል የሚኩራራና የሚተማመን ስለሆነ እውነተኛ የትግል ማዕበል ሕገ ወጥ ትግል መሆን የለበትምም፣ አያስፈልገውምም:: በመሆኑም ይህንን ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት ዴሞክራሲያዊ ለማድረግ በሚካሄደው የፖለቲካና የዲፕሎማሲ ትግል ተቃዋሚ ኃይሎችም ሆኑ ኅብረተሰቡ በምንም ዓይነት ይህንን ሕገ መንግሥት በሚፃረር ድርጊት መሠማራት አያስፈልገውም:: ሕብረተሰባችንን ከጎናችን አሰልፈን በሕዝብ ፈቃድ እስከንቀይረው ድረስ ሕግ አክብረን እንታገላለን ግን ደግሞ አንድ ሌላ ቁም ነገር አለ:: «በዴሞክራሲ ያልተከለከለ ነገር ሁሉ ይፈቀዳል በዲክታተር ደግሞ ያልተፈቀደ ነገር ሁሉ ክልክል ነው» ከሚለው መርህ እንነሳለን:: አፍ አውጥተው የለም እኛ ዲክታተር ነን ካላሉን በስተቀር በዚህ ሕዝባዊ ትግላችን ባልተከለከሉ የትግል ዘዴዎች ማለትም በሰላማዊ ሰልፍ፣ በሥራ ማቆም አድማና በሌሎችም የሲቪል ዲስኦቢዲያንስ ስትራቴጂዎች እንጠቀማለን ማለት ነው::

የሕብረቱ አማራጭ ፕሮግራም ለምሳሌ በዚህ በሕገ መንግሥት ጉዳይ ሰፊ ሕዝባዊና አገራዊ ውይይት እናካዳለን ይላል:: የሕዝብ ውይይት በሕገ መንግሥቱ አልተከለከለም:: ሕገ መንግሥቱ የሕዝብ ተመራጮች ለሕዝብ ፈቃድ ተገዢዎች ናቸው ይላል:: ይህንን የሕዝብ ፈቃድ ለማወቅ ሰፊውን ብሔራዊ ውይይት በሬፈረንደም እንቋጥረዋለን:: በሕገ መንግሥቱ ውስጥ ሕዝቡ ከፈለገ ፍላጎቱን በሪፈረንደም እንዳይገልጽ የሚከለክል አንቀጽ የለም:: ስለዚህ አካሄድ ዝርዝር ከኅብረቱ ሰነድ መረዳት ስለሚቻል አልገባበትም:: ባጭሩ ለማለት የምፈልገው አካሄዳችን ሕገ ወጥና በትጥቅ የታገዘ አመጽን አይጨምርም::

ጦቢያ:- ወደ ተቃዋሚዎች ሰፈር እንግባና በዚህ በሕገ መንግሥት ጉዳይ በዚህ ጎራ ያለው ሁኔታ ምንድን ነው?

ዶ/ር ነገደ:- በዚህ ጉዳይ ዛሬ በተቃዋሚው ሰፈር የተለያዩ አስተሳሰቦች አሉ:: በአንድ በኩል ሕገ መንግሥቱ መሻሻል ወይም መቀየር ያስፈልገዋል ወይስ አያስፈልገውም በሚለው የሕገ መንግሥቱ ይዘት ጥያቄ ላይ ልዩነቶች አሉ:: በሌላ በኩል ደግሞ ይሻሻል በሚሉት መካከል ምኑ ይሻሻል? እንዴት ይሻሻል? በሚለው ጥያቄ ላይ ልዩነት አለ:: በተለይ ውዥንብርና የደንቆሮ ጨዋታ ያለ የሚመስለኝ በዚህ በሁለተኛው ጥያቄ ነው::

ኢዴኃን በሁለቱም ጥያቄዎች ላይ በጣም ግልጽ የሆነ አቋም የያዘ ይመስለኛል:: ይህ ፀረ ዴሞክራሲያዊ ሕገ መንግሥት ተቀይሮ በሥልጣን ክፍፍል፣ በዳኝነት ነፃነት፣ በሕግ የበላይነት መርህዎች ላይ የተገነባ ዴሞክራሲያዊ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት ያስፈልጋል ይላል:: በቅርቡ ይፋ በሆነው አማራጭ ሰነዱ ይህንን አቋም በግልጽ አስቀምጦታል:: ዝርዝር የሕገ መንግሥቱ ይዘት በሕዝብ ፊት ክርክር እየተደረገበት የሚወሰን ስለሆነ የሕብረቱ ሰነድ እዚህ ውስጥ አይገባም:: ከዚህ ይልቅ ይህ የማሻሻል ወይም የመቀየር ሂደት እንዴት በሰላማዊ ሕዝባዊና ራሱን ሕገ መንግሥቱን ሳይቀር በሚጠቀም ሕጋዊ ዘዴ መካሄድ እንዳለበት የትግሉን ስትራቴጂ ይጠቁማል:: ዝርዝሩን ከራሱ ሰነዱ መመልከት ስለሚቻል አልገባበትም::

በሌላው ወገን ደግሞ ይህ ሕገ መንግሥት ምንም የሚወጣለት ነገር የለም፣ ችግሩ በአንድ በኩል ቀስ በቀስ እየተሸረሸረና እየተሸራረፈ መሄዱና በሌላ በኩል ደግሞ በወያኔ/ኢሕአዴግ በኩል ሕገ መንግሥቱን የሚጥሱ ሕገ ወጥ አሠራሮች መበራከታቸው ነው የሚል ኃይል አለ:: ሰሞኑን በዚህ መጽሐፍ ሳቢያ ከወጡት በርካታ ጽሑፎች መካከል «ሕዝባዊ» የተባለው የነ አቶ ገብሩ አስራት ቡድን ጋዜጣ ይዞ የወጣው አቋም ይኸ ነው:: በነዚህ ወገኖቻችን እምነት ሕገ መንግሥት ማሻሻልም፣ መቀየርም አያስፈልግም፣ ያለውን አክብሮ መሥራት ይበቃል:: መከራከር ስለሚቻል በዚህ አቋም ችግር የለኝም:: እርግጥ በመጽሐፉ ውስጥ በዚህ ጉዳይ በሰፊው ለማብራራት የሞከርኩት ነጥብ አለ:: ይህ ሕገ መንግሥት ለኢሕአዴግ ብቻ ሳይሆን የመንግሥት ለውጥ ቢመጣም አገራችንን «ለአላፊ አግዳሚው» ገዥ ፓርቲ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ አመቻችቶ ያስቀመጠ ሕገ መንግሥት ነው እላለሁ:: ከዚህም ተነስቼ በተቃዋሚዎች ሰፈር ሥልጣን ይገኙ አገራችንን በዚህ ሕገ መንግሥት አማካይነት አስተዳድ

ወደ ገጽ 18 ዞሯል

የምችለው። ኢሕአዴግ ቢመረጥ ደስተኛ ነኝ። ነገር ግን ሙሉ ለሙሉ ወንበር እንዲይዝ አልፈልግም። እኔ በግሌ የኢሕአዴግ ደጋፊ ነኝ። በተለይ በትግል ያሳለፉት ታሪክ ለኔ ትልቅ ቦታ አለው። ይሁን እንጂ እስካሁን ይህ ነው ብዬ የምመርጠውን አልወሰንኩም።

ጦቢያ:- እስካሁን ካልወሰንክ ምናልባት ምርጫህ ድምፀ ተአቅቦ ይሆን?

አቶ ነገደ:- እኔ ውስጥ ያለ እውነት አለ። ማድረግ የምችለውን መብቴን ለምንድነው የምተወው። በመምረጤ እጠቀማለሁ እንጂ አልጐዳም። በመብቴ በመጠቀም የማገኘው ትርፍ አለ። ያንን ትርፍ አላሳልፍም። ለማትረፍ ስል እመርጣለሁ።

በእርግጥ ካርድ ከወሰዱ በኋላ የማይመርጡ ሰዎች አሉ። አለመምረጥ መብት ቢሆንም ሀብት እንዳባከኑ ነው የምቆጥረው። ለካርዱ የወጣው ጉልበት፣ ካርዱን ለመውሰድ ያጠፉት ጊዜ ካሰብነው ብዙ ነው። አሁን ባለው ሁኔታ ግን ምናልባት የምርጫ ሰዓት እንዳይጠብ እንጂ ሕብረተሰቡ ከመምረጥ ወደ ኋላ ይላል የሚል እምነት የለኝም።

# «ሁሉም የካርዱን ዋጋ ማወቅ አለበት»

ብርሃነ ሥላሴ የኮምቦልቻ ነዋሪ

ጦቢያ:- የዘንድሮውን ምርጫ እንዴት ተመለከትከው?

አቶ ብርሃነ ሥላሴ:- አሁን እየተካሄደ ያለው የምርጫ እንቅስቃሴ ጥሩ ጐን ይታይበታል። ተቃናቃኝ ፓርቲዎችም ሆኑ ገዢው ፓርቲ በመገናኛ ብዙኃን ቀርበው መታየታቸው አንድ የእድገት ምልክት ነው። ይሄ እድገት እንዳለ ሆኖ ወደፊትም ተጠብቆ ኢትዮጵያ የራሷ የምርጫ ባህል እንዲኖራት ለማድረግ ትልቁ ተሳትፎ የሚጠበቀው ከሕብረተሰቡ ነው። ምርጫ መምረጥ አለብህ ሲባል ሕብረተሰቡ እንደ ዜጋ ያንን መብቱን መጠቀም መቻል አለበት። ለምሳሌ ካርድ ያወጣ ሰው የካርዱን ዋጋ ማወቅ መቻል አለበት።

ጦቢያ:- የምርጫ ግንዛቤ በደንብ ተፈጥሯል ማለት እንችላለን?

አቶ ብርሃነ ሥላሴ:- ይህ ነው የሚባል ግንዛቤ አለ አልልም። በመጀመሪያ የከተማው ሕዝብ ከአጠቃላይ አሥራ ስድስት ፐርሰንት ያህል ነው። ስለምርጫ ትክክለኛ የሆነ መረጃ ይደርሰዋል የሚል እምነት የለኝም። ለምሳሌ የገጠሩ ሕብረተሰብ ስለምርጫው ግልጽ የሆነ መረጃ የለውም። ግን አጀማመሩ ጥሩ ነው። ለሚቀጥለው ትውልድና ለሚቀጥሉት ጊዜያት ፈር ቀዳጅ ይሆናል።

ጦቢያ:- ዲሞክራሲያዊነቱስ?

አቶ ብርሃነ ሥላሴ:- ኢትዮጵያ ውስጥ ፖለቲካ የሚፈራበት ሁኔታ አለ። ነገር ግን ያ ዝምታ ተሰብሮ በመገናኛ ብዙሃን መንግሥትን ሲቃወሙ እናያለን። ይህ አንድ ተሞክሮ ነው።

ጦቢያ:- ምርጫውን አስመልክቶ በተለያዩ መድረኮች ይካሄዱ የነበሩት የፖለቲካ ፓርቲዎች ክርክሮች ሕዝቡ የሚመርጠውን እንዲያውቅ አስችለውታል ብለህ ታምናለህ?

አቶ ብርሃነ ሥላሴ:- አንዳንድ ድክመቶች ታይተውበታል። አንዳንዶቹ ክርክሮቹ ሕዝቡን የሚጠቅሙ፣ የሕዝቡን ጉዳይ የሚያነሱ አልነበሩም። የሚበጀውን በእርጋታ ከማስረዳት ይልቅ ስሜታዊነት ተንፀባርቆበታል። በዚህም ሕዝቡ ውዥንብር ውስጥ እንዲገባ ሆኗል። ይህ ደግሞ ፓርቲዎችን ጥርጣሬ ውስጥ የሚከት ነው።

ጦቢያ:- አንተስ የምትመርጠውን ወስነሃል?

አቶ ብረሃነ ሥላሴ:- የምመርጠውን ገና እየገመገምኩ ነው። እስካሁን አንድ ውሳኔ ላይ አልደረስኩም። እውን ተቃዋሚ ፓርቲዎች የተነሱበት ዋና ዓላማ ሕዝቡን ለማገልገል ነው ወይንስ ለሌላ? እንዲሁም ገዢው ፓርቲስ ምን አዲስ ነገር አለው የሚለውን እያየሁ ነው።

ጦቢያ:- የምትጨምረው ካለ?

አቶ ብረሃነ ሥላሴ:- አንዳንድ ሰዎች ተቀናቃኝ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ብመርጥ ምናልባት የመንግሥት አካል ያየኝና ነገ አንድ ችግር ይመጣብኛል የሚል ፍርሃት አላቸው። ከዴሞክራሲያዊ ምርጫ ግንዛቤ እጥረት የሚመነጭ ነው። ይህ ፍርሃት ብዙ የምርጫ ካርዶችን ሊያባክን ይችላል።

## መኢሶንና...

ከገጽ 15 የዞረ

መምሪያ በየቦታው ተበትነው በመኖሪያ ቀበሌያቸው ተሰማርተው በቀይ ሽብር ሂደት ቀጥተኛ ተሳታፊ እንዲሆኑ ለተካ ቱሉ መመሪያ አልሰጡም?» እያሉ ትንኝ ገድዬ አላውቅም እያሉ የሚቀጥፉትን መንግሥቱ ኃይለማርያምን የ«ቀይ ሽብር» ቁንጮ ተዋናይ እንደነበሩ ያጋልጣሉ። እኝህ ውስጥ አዋቂ ሠደድንና የወዝ - ሊግን ከ«ቀይ ሽብር» ጋር ሥማቸውን አያይዘው ሲጠቅሱ መኢሶንን አንድም ቦታ ላይ አልጠቀሱትም። ግን ለምን? የለበትማ!!!

ማንም ለማረጋገጥ እንደሚችለው የመኢሶን መፈክር «የነቃ የተደራጀና የታጠቀ ሠፊ ሕዝብ ያሸንፋል!!» የሚል ነበር። ያልነቃና ያልተደራጀ ሕዝብ ቢታጠቅም አብዮቱን ከግቡ ሊያደርሰው እንደማይችል በፅኑ ያምናል። ስለዚህ በትግሉ ወቅት አተኩሮ የነበረው ሕዝብን በማንቃትና በማደራጀት ላይ ነበር። የመኢሶን አመራር የጦር መሣሪያ ባልነቃና ባልተደራጀ የሕብረተሰብ ክፍል እጅ ከገባ አጥፊ እንደሚሆንም ጠንቅቆ ያውቅ ነበር። አባሎቹም በዚሁ መንፈስ የተገሩ ስለነበሩ ቃታ ለመሳብ ጣታቸውን የሚበላቸው (TRIGGER HAPPY) አልነበሩም። ትምህርትና የሕይወት ተሞክሮ ያለዘባቸው፣ ለችግሮች መፍቻ የፖለቲካን መፍትሔ እንጂ የጦር መሣሪያ መጠቀምን የማያስቀድሙ ነበሩ። አንዳንዶቹ ሊሰሏቸው እንደሚፈልጉት የወሮበላ መንጋ አልነበሩም። ቡዙዎቹ የቤተሰብ ኃላፊ የነበሩ ከሁሉ ነገር በላይ ለሰው ልጅ ሕይወት ዋጋ የሚሰጡ ነበሩ።

አሁን አሁን የውዥንብሩ ጊዜ እየጠራ የመጣ ይመስለኛል። አቶ አንዳርጋቸው አሰግድ «በአጭር የተቀጨ ረጅም ጉዞ» ብለው በሰየሙት መጽሐፋቸው መግቢያ ላይ «እውነት በጭጋግ እንደተጋረደ ተራራ ነው። ጭጋጉ ሲለቅ ታዲያ! ተራራው የነበረ፣ ያለ፣ የሚኖር መሆኑን በሙሉ ግርማ ሞገሱ አውጆ ይታያል። ጭጋጉ ከርሱ ፊት (በራሱ ላይ) ደርሶ ከቸች ይልና አላፊ የተፈጥሮ ክስተት ሆኖ ይተናል። እንደውሸት።» ብለው ነበር። አሁንም ቢሆን የፖለቲካው ዳፍንት ምሑሩንም ሆነ ሌላውን ሲለቀው፣ የመኢሶን ዕውነተኛ ማንነት ፍንትው ብሎ ይወጣል።

ከእንግዲህ ወዲያ ያለፉት ታጋይ ምሁራን ያለቁት ለቁም ነገር ሲታገሉ ሳይሆን በመናኛ ልዩነት ማለትም በእሸነፈና በአቸነፈ በሚል ቃል ተለያይተው ወይም ደግሞ ወዝአደርና ላብአደር በሚል ልዩነት ተለያይተው እርስ በርሳቸው ስለተጨፋጨፉ ነው የምትሉት ሀሰተኛ ወሬ ተቀባይነት አይኖረውም። ዕውነቱን መናገር መጀመር ያለብን ይመስለኛል። መኢሶን ያጠፋውም ነገር ካለ ከማስረጃ ጋር በግልጽ ቀርቦ እንነጋገርበትና እንዳንደግመው እንማርበት። የሠራውም መልካም ሥራ እንደዚሁ ተነግሮ ወጣቱ ትውልድ እንደ አርአያ የሚወስደው ነገር ይኑረው። አለበለዚያ ሀሰትን ባስፋፋን ቁጥር ወጣቱን ትውልድ አርአያ እንዳይኖረውና ከአገሩ ጉዳይ «ፖለቲካና ኮረንቲን በሩቁ» ብሎ እንዲሸሽና አገርም አለኝታ እንድታጣ ያደርጋል። ለሕዝባችን ዕውነቱን ማስተማር ካልቻልን፣ ገዢዎቻችን ብቻ ሳይሆኑ ሕዝባችንን የሚበድሉት እኛም ጭምር መሆናችንን መዘንጋት የለብንም። ያለፉትን ታጋዮች በመኢሶንም በኩል ሆነ በኢሕአፓ በኩል ተሰልፈው የተሰውትን እህት ወንድሞቻችንን ባነሳሰን ቁጥር መጪውን ትውልድ በአገር ፍቅር አንጾ ለማሳደግ ትልቅ ችግር የሚገጥመን ይመስለኛል። ዕውነቱን እንመርምር፣ ዕውነቱንም እናስተምር፤ ያኔ ፀረ-ሕዝቦችን የሚዋጋ ትውልድ እናፈራለን!!!

በተረፈ እንደ ዶ/ር ነገደ ጐበዜ ያሉ ታጋይ ምሁራንን በርቱ፣ መንገድ <ጠቋሚ> የሆነውን ምክራችሁን አትንፈጉን ስል እሰናበታለሁ። መልካም ዕድል ለሕዝባችን!

## «ሰሳፋሪ...

ከገጽ 13 የዞረ

ራሱሁ የሚል ኃይል ካለ ይህንን ኃይል «እንደ ዛሬ ተቃዋሚና እንደ ነገ ፈላጭ ቆራጭ ገዥ» ቆጥሮ ከወዲሁ መታገል ያስፈልጋል ብዬ ለማስጠንቀቅ ሞክሬያለሁ። ከነዚህ ወገኖቻችን ጋር ግልጽ የእይታና የፖለቲካ ልዩነት አለ ማለት ነው። ሆኖም እኛ የምንለው በሕገ መንግሥቱ ጉዳይ ራሱም ኢሕአዴግም አቋሙን እንደያዘ ሰፊ ብሔራዊ ውይይት ይካሄድ ስለሚባል ችግር የለም። ድሮም ዴሞክራሲያዊ ውይይትና ክርክር ነው የምንጠይቀው።

በሁለቱ መሃከል ደግሞ እንደ ቅንጅቱ ያሉ ኃይሎች አሉ። ሕገ መንግሥቱ መቀየር አለበት ይላሉ። እንዲያውም በቅርቡ ባወጡት የምርጫ ማኒፌስቶ ይሻሻላሉ የተባሉትን የሕገ መንግሥቱ አንቀጾችና ንዑስ አንቀጾች ስቆጥራቸው ከሃምሳ በላይ ናቸው። ከነዚህ ውስጥ ጨርሶ የማልስማማባቸው በጣም በርካታ የማሻሻያ ሃሳቦች አሉ። በተለይ ስለ ሥልጣን ክፍፍል፣ ስለ ዳኝነት ነጻነትና ስለ ፓርላማው ሚና የሚያቀርቡት ሃሳብ እስከ ናካቴው አንቀጽ 50ን የሚያጠናክር ሆኖ አግኝቼው ትንሽ ግራ ገብቶኛል። ዴሞክራሲያዊ ሕገ መንግሥት ካልን በአካሄዳቸው መስማማት አይቻልም። ግን ዛሬ ያለንበት ሁኔታ እንኳን 50 ቀርቶ የወያኔን ሕገ መንግሥት የአንዲት ንዑስ አንቀጽ ዝንብ እሽ ልንል የምንችልበት ሁኔታ ላይ አይደለንም። ስለዚህ ሴትዮዋ «ቀድሞ ባሉን» እንዳለችው ነው። ስለ ይዘቱ ከመከራከር በቅድሚያ ተጋግዘን ሕገ መንግሥቱን ለማሻሻል የሚያበቃንን ሁኔታ መፍጠር አለብን። በዚህ በኩል የቅንጅቱ ወገኖቻችን እምብዛም የሚሉት ነገር የለም።

ኅብረቱ ባቀረበው አማራጭ ሰነድ ሕገ መንግሥቱን እስክንቀይር ድረስ አንዲትም ከሕገ መንግሥቱ አንቀጾች ተፃራሪ የሆነች ፖሊሲ አይሰነዝርም። ከዚህ ጀርባ ያለው ፍልስፍና ሕጉን እስክንቀይር ድረስ በሕጉ መሠረት መሥራት እንገደዳለን አለበለዚያ ለወያኔ አመጽ በር መክፈት ይሆናል የሚል ፍልስፍና ብቻ አይደለም፣ የማይሆን ነገር ለሕዝባችን ቃል መግባት የለብንም ከሚለው ሃቀኝነትም ተነስተን ነው።የቅንጅቱ ማኒፌስቶ ለምሳሌ መሬት የመሸቀጥና መለወጥ የሚል ፖሊሲ ለሕዝቡ ቃል ይገባል። በበኩሌ አንድ ድርጅት የራሱን ፖሊሲ በመቀየሱና በማስታወቁ ችግር አይታየኝም። ግን ይህንን ፖሊሲ በተግባር ለማዋል የግድ ሕገ መንግሥቱን መቀየር ስለሚያስፈልግ ይህ እንዴት እንደሚሆንም ድርጅቱ ያለውን ስትራቴጂ አስቀድሞ በግልጽ ማስቀመጥ ይኖርበታል። የተባለውን አንቀጽ ቀይሮ የቅንጅቱን ፖሊሲ በተግባር ለማዋል በሁለቱ ሻምብሮች ሁለት ሦስትኛ ማጆሪቲ አይበ

ወደ ገጽ 24 ዞሯል

ይድረስ ለክቡር ወንድሜ፣ መልእክት አለኝ ለባድሜ ሕዝብ
የምታስተላልፍልኝ፣ የተላከ ብለህ ከልብ::
መሪው በሕዝብ ስም ዋሽቶ፣ ሞታብናለችና አገር
የባድሜ ዝብሬ ራሱ፣ ቁርጡን ባለአገር ይናገር::
ምሁሩና ተቃዋሚው፣ ተጠላለፈና እንደእሠር
ለመደበትና ከህደት፣ የወንጀል ጣት መቀሣሠር
ጠፋብን ሀቅ የማናገር::

ኑሮ ከጉድጓድ ባይጠብቅም፣ ከወገን ጠላት አይቀርብም
የሆድ ነገር ሆድ ቢቆርጥም፣ ከእናት አገር ሆድ አይብልጥም::
እና ባለአገር ይንገረው፣ ለአዲሳባው የወኔ ስልብ
ቤቱን ትዳሩን ባለፎቅ፣ ላፈረሰበት ብኩን ሕዝብ
አሻፈረኝ ማለት ፈርቶ፣ ለሚንከራተት ያለ ልብ፤
አምን ባለአገር ይንገረው፣ ያልተብከለው መንፈሱን
መቶ ጊዜ ባንዳ ቢያንቀው፣ የማይተነፍሰው ሀቁን
ዝብሬው ራሱ ይናገር
ምሁርና ተቃዋሚው፣ ተጠላልፎ ከሚገተር::
ለግማሽ ምዕተ ዓመት፣ አፍ ሲካፈት እንደቁራ
አገር ያስገደለው ምሁር፣ ወንጀሉን በብጤው ጉራ
ከማላከክ በስተቀረ፣ ጥፋቱን መቀበል ላይችል፣
ዛሬም ባድሜን አስገድሎ፣ ጥፋተኛ እኔ ነኝ ሳይል
ሊያዘናጋ ይራራጣል፣ አከሰም ሀውልት ሊያስተክል
የገደለው አገር ከሞት፣ በድንጋይ ይነሳ ይመስላል!
ስለዚህም ባለአገሩ፣ የአገሪቱን ሀቅ ይመስክር
እቅጩን ሳያደናግር
የፍርሀትን የሞት ጥላ፣ ይግፈፍልን ከእናት ምድር
የሱን ጩኸት እኛ ነጥቀን፣ ከምንቀር ጣት ስንቀስር!

ዘውድም ኖሮ ከርሞ ሄዷል፣ እኛ ቀርተን ጣት ስንቆጥር
ደርግም ኖሮ ከርሞ ሄዷል፣ እኛ ቃላት ስንደረድር
ወያኔም አሥራ አራት ዓመት፣ በስብሷል ፊደል ስንጭር
ስለዚህ ተራው ነው ዛሬ፣ ባለአገር ቆርጦ ይመስክር
ለወያኔ በማይገባው፣ በቋንቋው ሀቁን ይደርድር::

ይድረስ ለባድሜው ጠፍ ዜጋ፣ እኛን ምሁራኑን ፍራ!
ባህር በራችንን ዘግተን፣ ሽራተን ቧልት ስናደራ
የባድሜን ትውልድ ገድለን፣ በአጥንቱ የምናጓራ
እኛን ፍራ ምሁራኑን፣ የስድስት ኪሎ ተውሳኩን
የምክር ቤቱን አፋሙን፣ የምርጫ ቦርዱን ዝግ አፉን
ጭንቅላታችን በቅድሚያ፣ የሞተብን ዕኩያኑን
ሆዳችን ብቻ ለቀረው፣ የእናት አገር ድውያኑን
ሞት ለወጣት የምንዘራ፣ ስግብግብ የሥልጣን ቁራ
እኛን ሆድ አምላኩን ፍራ!
በቁራሽ ሥልጣን እንጀራ፣ ፎቃችንን ልንሠራ
አንተን «ብነፃ ገበያ»፣ ሸጠን ልንረግጥ ዳንኪራ
እንደታቦት በአታችን፣ ጭራቅ የጫንነውን ጭብራ
ድምፅ መስጫ ኮሮጆህን፣ የሰጠን ለጠላት ጉራ
ሽብልቀን የምንበላ፣ የሰማዕታቱን አደራ
የዘመኑን ላሊበላ፣ የኢትዮጵያን ፈንጋይ ደላላ
የዘመኑን ግብረ በላ፣ የአሮጌን ደርግ ቱልቱላ
የአዲስ ወያኔን ቡችላ፣ የተገዛነውን ለእርስ
ለብሌር ቅኝ ግዛት ሠርግ፣ ለመለስ የቅልቅል መልስ
የቱጃሮቹን ቡችሎች፣ የምናጓራውን በፈርስ
ከዲሲ ውቤ በረሀ፣ እስከአዲሳባው ሽራተን
አትላንቲክን ተረማምደን፣ አሰብና ባድሜን ሸጠን
ያንተን ሰብዕና ገድለን፣ በመወንጃጀል መከር
ጣት ለጣት በመቀሣሠር፣ ቆመን የሸጥነውን አገር
ወንድምዬ እኛን ፍራ፣ የአዲሱን ዘመን ጓጉንቸር::

ይድረስ ለተሸጥከው ዜጋ፣ ወገን ለጣለህ ያለአጋር
እንደጉደለ ቀን ትንቢት፣ እንደሚያገዛው ንግርት አድባር
አበቅቴህ ብትጨልምም፣ ታሪክህ ግን ይወጣል ዳር::
ጊዜ በጊዜ እንደሚሻር
ዘር ከልጓም እንደሚስብ፣ እንደርካሽ ባለጌ ዛር
በባህርይ ቅርፀታቸው፣ ልክ እንደቲአትር ቢጋር
ሂትለርና ሙሶሊኒ፣ አንድ ናቸው ከመለስ ጋር::
ውድቀታቸውም አንድ ነው፣ ውጉዝ እንደሣጥናኤል ጣር::
ሦስቱም እንደእንጦርጦስ ውርድ
ሕዝብን በሕዝብ በመዳጥ፣ በማጨፋጨፍ እንደዕብድ
አገር ከፋፍሎ በመግደል፣ እንደሰይጣን ውላጆች ፍርድ
አንዱን ወገን እየካቡ፣ አንዱን በመቆረጥ እንደግንድ
ሂትለርና ሙሶሊኒ፣ መለስም እንደጣቃ ቅድ
በባለጌነት አፍ ከፍተት፣ እንዳልተቆነጠጠ ውልድ
ሕዝቡን «ጨርቅ» ነህ በማለት፣ በመሳደብ ልክ እንደስድ
አንድ ናቸው በምላስ ልምድ::
እንደተራራ ላይ ኮረት፣ ናዳ የማሽቀልቀል ግብሩ
ተፈጥሮአቸው ሆኗልና፣ አይከብዳቸውም ነውሩ::
የሕዝብን የአንድነት ማተብ፣ በእርኩሰት እያገለሙ
ሲያላጭቁ እንዳጫት ዱቃቅ፣ ሕዝቡም ይጉመራል ደሙ፣
ይሟጠጥበታልና፣ ውርደት የመቀበል አቅሙ::
ሕዝቡ መቃብሩን ጥሶ፣ እንደአባቶቹ በቅስሙ
እንደሂትለር አሻራ ቀን፣ ሲደፋ መለስ አዚሙ
ወንድምዬ አትጠራጠር፣ ታሪክ ራሱን ለመድገሙ::
ስለዚህም ተቃዋሚው፣ በአንድነት በመፅናት ፋንታ
እርስ በርሱ ተጠላልፎ፣ በድል በራፍ ላይ ሲፈታ፣
ሦስተኛ ዙር የሕዝብ ውርደት፣ ለወያኔ ሠንጋ ፈረስ
የጮሌነት ጭድ መደገስ
ተቃዋሚዎች ነን ብለው፣ ሕዝብን ተቃውመው ማናከስ
አማራጭ በሌለው ምርጫ፣ ገዢውን መለስ ለማንገስ
በሕዝቡ ስም የሕዝቡን ድል፣ እስከነራዕዩ ማፍረስ
ህብረቱን በእልህ ማልኮስኮስ

ይድረስ ለባድሜው ጠፍ ዜጋ፣ ወንድምዬ እንዴት ከረምክ?
ከዘር እንደተፈነቀልክ፣ ለሸያጭ እንደተጠፈርክ
በሰንሰለት ተቀፍድደህ፣ ቋንቋህን እንደተቆረጥክ
መፈጠርክን እንደረገምክ
ማንነትክን ምንነትክን፣ በታሪክ ሞት እያስታመምክ::
ለአዲስ ተስፋ ጉህ ፈነጠቅክ፣ ወይ በሕይወት ተስፋ ቆረጥክ?
ለሕዝብ ድል ብርሃን ሠረፅክ? ወይስ ራዕይህን ገደልክ?
...ወንድምዬ እንዴት ከረምክ?...
የግፍ ከራሞት ብትከርምም፣ የታሪክ ፈለግ ብቅሉ
እየቀል ነውና ምርቱ፣ አበቅቴው አብቃቀሉ
ባንተ ስም ነውና ዛሬ፣ ዓለም ኢትዮጵያን ማቅለሉ
ለእናት አገር ስትል ፅና! ማተብህን አታላላ
መቃብርክን ሰብረህ ንቃ! ኢትዮጵያዊነትክን አስላ
ወንድምዬ እምቢ በላቸው፣ ሞትክን አሸንፈህ አክላ!
የባርነትክን ሰንሰለት፣ በጥሰህ ውጣ እንዳዐለላ!

ይድረስ ለክቡር ወንድሜ፣ ይድረስ ለባድሜው ጠፍ ዜጋ
አትጨልምም ያሏት ፀሐይ፣ በውርደትህ ቀን ስትነጋ
ክብርህ ምንኛ ቀለለ? ልብህ ምንኛ ተወጋ?
ይድረስ ለክቡር ወንድሜ
ታሪክ እንደሉጥ ዘመን ሴት፣ ተሽርከታ ባንተው ዕድሜ
ትላንትና በጀግኖች ደም፣ የተቀዳጀኸውን ድል
ያለአንተ ፈቃድ በፊርማ፣ ስንፈነግላት በግፍ ውል
ከነአፈርህ ከነአጥንትህ፣ ስንሸጥህ አንተንም ጭምር
ምንኛ መርገም ተሰማህ፣ ወንድሜ ንገረኝ በምር?
በኛማ በቃል ጦር ሜዳ፣ በመጣጥፍ ትንቢት አልፋ
ወንጀለኛው እንደዳኛ፣ ወሳኝ ቀለም እየደፋ
የሃይማኖት አባት ሁላ፣ ዘረኝነት እያስፋፋ
ጦር አዛዡም እንደአራጅ ዛር፣ ቀርበታውን እየነፋ
ጮሌም በጋዜጠኛ ስም፣ ውዥንብሩን እያፋፋ
ተቃዋሚም ጉራ ባክኖ፣ መቶ መግለጫ እየተፋ
ባድሜ እንደሉጥ ብትደፋ
ለወያኔ ተመችው እንጂ፣ ገዢነቱ መች ተከፋ?
እየሸጠህ በመሸጦ፣ እንደፋጉሎ ፈግሞ
ከነአፈርህ ከነአጥንትህ፣ ትግራዊነትህ ላይ ቆሞ
ያለአንዳች ህሊና ፀፀት፣ «ምረጠኝ» ይልሀል ደሞ!
ይድረስ ለክቡር ወንድሜ፣ ይድረስ ለባድሜው ጠፍ ዜጋ
መለስ በጆሮህ ያስጮኸው፣ የውሸት ሰላም አለንጋ
በምድር ዓለም ሲዘረጋ
አይጨልምም ያሉህ ጀንበር፣ በውርደትህ ቀን ላይ ነጋ!
ወንድምዬ ሺህ ጊዜ ሞትክ፣ ልብህ ሺህ ጊዜ ተወጋ!

በቸር ይግጠመን::

## «ሕሳፋሪ...

ከገጽ 18 የዞረ

ቃም:: በሁሉም ክልሎች ምክር ቤቶችም ማጅሪቱ ማምጣት ያስፈልጋል:: ባጭሩ አንድ አናሳ ኃይል የተከለብንን ሕገ መንግስት ለማሻሻል «ሕገ መንግሥታዊ ኩዴታ» የሚል አጉል አካሄድ ኀብረቱም ቅንጅቱም የሚስማሩ አይደሉም:: ይህ ካልሆነ ደግሞ ያለን አማራጭ ድፍን አገርን ማንቀሳቀስ አለብን ማለት ነው:: ኀብረቱ የሚለው ይህንን ነው:: ለዚህ ደግሞ ልክ መድበለ ፓርቲ ሥርዓት ውስጥ ያለን ይመስል ሁሉም «ይኼ ነው ፕሮግራሜ ምረጡኝ» እያለ የትም ለማያደርስ ሂደት አማራጮችን ከማንጋጋትና ሕዝብ ግራ ከማጋባት በጋራ ጊዜያዊ ፕሮግራምና በጋራ ትግል ጎዳና መሠማራት ያስፈልጋል:: ቀጣይነትና ተአማኒነት ያለው አገር አቀፍ እንቅስቃሴ ፈጥረን ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመሸጋገር የምንችለው ዛሬ በፖሊሲ ልዩነት ኃይልን በመበታተን ሳይሆን በምርጫው ሂደት ተጠቅመን በፖለቲካውም በዲፕሎማሲውም መስክ ቀጣይነት ያለው የጋራ ትግል ስናካሂድ፣ ብቻ ነው::

ጦቢያ:- አሁን እስኪ ወደ ምርጫው ጉዳይ እንግባ:: የመንግሥት አንዱ ቅስቀሳ «ትላንት የደርግ አይድዮሎጂ ቀያሽ የነበሩት ዶክተር ነገደ ዛሬ ደግሞ የተቃዋሚዎች የምርጫ ስልት ጠንሳሽ ሆነዋል» የሚል ነው:: ጠንስሰዋል ወይ? የጠነሰሱትስ ስትራቴጂ ምንድን ነው?

ዶ/ር ነገደ:- እዚህም ላይ እንደ ሕገ መንግሥቱ ጥያቄ ነው:: ከፍ ብዬ እንዳልኩት ዛሬ በአገራችን የዳኝነት ነፃነት የለም፤ ዛሬ በሀገራችን የሕግ የበላይነት የለም፤ ዛሬ በአገራችን ፓርላማው የበላይ አካል ተባለ እንጂ የነ አቶ መለስ ፍጡርና መሣሪያ ነው የሚለውን እውነታ ሁሉም ያውቀዋል:: እኔ ያደረግሁት ነገር ቢኖር የዚህን ሁሉ ቴዎሬቲካል ጅርባ አቀነባብሮ ማቅረብ ነው:: በምርጫውም «ስትራቴጂ» በኩል በእውነቱ ነገሩን አቀነባብሬ አቀረብኩት እንጂ እንደ እኔም ሆነ እንደ ድርጅቴ መኢሶን ከድርጅት ይልቅ የአገር አጀንዳ የሚያስቀድሙ የተደራጁም ያልተደራጁም ዜጎች በሙሉ ከዳር እስከዳር የሚሉትና የሚጠይቁት ስትራቴጂ ነው:: የፈጠርኩት ምንም ነገር የለም:: ሁሉም ተቃዋሚ ኃይሎች በየምርጫ ወረዳው አይደራረቡ ይላል:: እኔም የማቀርበው «ስትራቴጂ» እንደዚሁ የጋራ ተወዳዳሪዎች የሚል ሲሆን ይህ ለምን መሆን እንደሚገባው፤ በዚህ «መድበለ ፓርቲ» ሳይሆን «መድበለ እንቅፋት» ብዬ በጠራሁት ሥርዓት ሥር ለየብቻ ተወዳድሮ ለማሸነፍ የምርጫ ሥርዓቱ ለምን እንቅፋት እንደሚሆን፤ ከወያኔ የተለየ ፖሊሲ የሚከተሉ ኃይሎች በተአምር ቢያሸንፉ እንኳን ይህ ድል የትም እንደማያደርሳቸው በሰፊው እየተነተንኩ ለማስረዳት ሞክርኩ እንጂ «ስትራቴጂው» ሥፍር ቁጥር የሌለው የአገራችን ዴሞክራቶች የሚያራምዱት ስትራቴጂ ነው::

ጦቢያ:- ከዚህ አንፃር የምርጫውን እንቅስቃሰ እንዴት ይመለከቱታል? አንዳንዶች እንዲያውም ከዚህ ሂደት በአሸናፊነት እንወጣለን የሚሉ አሉ:: ተቃዋሚዎች በዚህ ምርጫ የማሸነፍ እድል አላቸው ወይ?

ዶ/ር ነገደ:- በመካሄድ ላይ ያለው እንቅስቃሴ በጣም የሚያኮራ እንቅስቃሴ ነው:: ካለፈው ምርጫ በላቀ ሁኔታ ተቃዋሚ ድርጅቶች ባደረጉት ጥረትና ኀብረቱም፤ ቅንጅቱም፤ ሌሎችም ድርጅቶች መስዋዕትነት እየከፈሉ ባካሄዱት ትግል ዛሬ ሕዝባችን በመላ በአገሪቱ ለለውጥና ለዴሞክራሲ የሚያደርገው እንቅስቃሴ ወያኔ ኢሕአዴግን ብርክ እንዲይዘው

ወደ ገጽ 32 ዞሯል

## «እሳፋሪ...

ከገጽ 24 የዞረ

አድርጎታል:: ይህንን ሁሉ ስመለከት ተቃዋሚ ኃይሎች በመላ በአገሪቱ የሚያገኙት ድምጽ ቢደመር ከሃምሳ ከመቶ በላይ እንደማይሆን እገምታለሁ:: ግን ደግሞ «መልሶ ቀልሶ ወልደ አረጋይ ለቅሶ» ባትሉኝ ወደ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት ልመልሳችሁ::

ከፍ ብዬ ስለ ሕዝብ ድምጽ ተደማጭነት ያልኩት ነገር አለ:: ሕዝባችን ታግሎ፣ ተሰውቶ ባካሄደው ትግል በአገሪቱ ደረጃ ማጀሪቷ ድምጽ ሊያመጣ ይችላል:: ነገር ግን አብላጭ ድምጽ በተባለው የወያኔ ሕገ መንግሥት የምርጫ ሥርዓት የተነሳ ከፓርላማ ማቀመጫ አንፃር ይህንን በመስዋዕትነት የተገኘ ድል ሊቀማ ይችላል:: እኔም፤ መኢሶንም፤ በጠቅላላው የአገራችን ዴሞክራቶች ደግመን ደጋግመን «የጋራ ተወዳዳሪዎች» ያልነው የሕዝቡ ድል በዚህ የምርጫ ሥርዓት እንዳይቀማ ነበር:: ይህ የጋራ ተወዳዳሪዎች ጥሪ ተቀባይነት አላገኘም:: በመጽሐፉ ውስጥ ያስተጋባሁት ሕልመኛው አቋሜ በ547ቱም ወረዳዎች «እኛና እነሱ» ብለን እንፋለም፤ ከወያኔ ፊት አንድ ተቃዋሚ ብቻ ይሰለፍ፤ በግለሰብ ተወዳዳሪነት ስም ለሚሰለፉብን ለወያኔ ሰርጎ ገቦች በር ለመዝጋት የተቃዋሚዎች የጋራ ፕላትፎርም አዘጋጅተን በአካባቢያቸው ተቀባይነት ሊያገኙ የሚችሉ ግለሰቦችንም ይህንን ፕላትፎርም እስከ ተቀበሉ ድረስ በተቃዋሚው ጎራ ተወዳዳሪነት የሚገቡበት ሁኔታ እናመቻች የሚል አቋም ነበር:: ይህ አቋም ተቀባይነት አላገኘም::

ዛሬ በአዲስ አበባ ብንሄድ ለክልል 23 መቀመጫዎች ኢሕአዴግ 23 ተወዳዳሪዎች አቅርቡዋል:: ተቃዋሚዎች ደግሞ 187 ተወዳደሪዎች አቅርቧል:: የተቃዋሚው ጎራ ድምጽ 187 ቦታ ይከፋፈላል ማለት ነው!! ይበተናል ማለት ነው!! እነ አቶ ልደቱ አያሌው በሚወዳደሩበት ወረዳ ለምሳሌ ትምህርት ሚኒስትሯን ወይዘሮ ገነት ዘውዴን «የሚፋለሙት» አስር ተቃዋሚዎች መሆናቸውን ባለፈው ጦቢያ መጽሔት አንብቤያለሁ:: በዚህ መጽሔት አቶ ልደቱም፣ ዶክተር መረራም «ወያኔ ሆን ብሎ በጠነሰሰው ሤራ የተቃዋሚውን ድምጽ ለመበታተን በግለሰብ ተወዳዳሪነት ስም ሰርጎ ገቦች መሰማራታቸውን ደርሰንበታል፣ ማስረጃ አለን» ብለውናል:: ይህም ወንዝ የማያሻግር መከራከሪያ አይደለም:: ዜጎች አትወዳደሩ አይባልም:: በቀረበው ሃሳብ መሰረት «እኛና እነሱ» በሚል ሂደት ለሰርጎ ገቦች በሩን መዘጋት ይቻል ነበር:: አዲስ አበባን በምሳሌነት ጠቀስኩ እንጂ ይህ ክስተት በያለበት ያለ ነው:: እገሌ አጠፋ እገሌ ለማለት አይደለም:: በዚህ ሁኔታ በትግላችን ላይ የደረሰውን ጉዳት ለመረዳት ስለባከነው የሕዝብ ድምጽም ትንሽ ግንዛቤ ለማግኘት የነ አቶ ልደቱንና የወይዘሮ ገነትን ቀበሌ 547 ጊዜ ማባዛት ነው!! በዚህ ስሌት ስንሄድ ሕዝቡ ለተቃዋሚዎች የሚሰጠው ድምጽ ሲደመር ከ50% በላይ ሊሆን ይችላል:: ግን በያለበት የኢሕአዴግ ተወዳዳሪ ሰላሳም፤ ሰላሳ አምስትም ከመቶ እያገኘ ተመረጠ ተብሎ ፓርላማ ውስጥ ኢሕአዴግ ማጆሪቲ የሚሆንበት ሁኔታ ውስጥ ነን ማለት ነው::

አነጋገሬ የብሽቀት ሊመስል ይችላል:: ጨርሶ ግን የተስፋ መቁረጥና የተስፋ ማስቆረጥ አነጋገር አይደለም:: እኔ የግንቦቱ ምርጫ ውጤት እስከዚህም አስጨንቆኝ አያውቅም:: ዋናው ጥያቄ ቀጣይነትና ተአማኒነት ያለው አገር አቀፍ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ እምርታ መቀስቀሱ ላይ ነው:: ተቃዋሚ ድርጅቶች ባደረጉት ጥረት ዛሬ ይህ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ተፈጥሯል:: እነዚህ ድርጅቶችም በውጭም በውስጥም ያሉ የአገራችን ዴሞክራቶችና ከሁሉም በላይ ደግሞ ሕዝባችን ሊኮራ ይገባል:: ከሁሉም በላይ ግን በዚህ ድል ላይ የመገንባቱ ተግባርና አገራዊ ግዴታ አለ:: ጥሩ ሳልም ያደርኩ እንደሆን ተቃዋሚ ድርጅቶች ይህንን ኃላፊነት ተቀብለው፣ ድርጅታዊ አጀንዳን ወደ ጎን አድርገው ይህ ሕዝባዊ ኃይል ቀጣይነትና ተአማኒነት እንዲኖረው በምርጫ ማግስት አገር አቀፍ ጉባዔ ሲቋጥሩት ይታየኛል:: ሲያቃገፕኝ ሳድር ደግሞ እንዳለፈው ጊዜ ይህንን ትግል በትነው ዛሬ በወያኔ ካድሬዎች እጅ ይህ ነው የማይባል አፈና፤ ግድያ፤ ወከባ እየተካሄደበት እሱን ተጋፍጦ በግንባር ቀደምነት የሚንቀሳቀሰውን ዜጋ ለቀጣይ የአፈናና የወከባ ውርጅብኝ አጋልጠውት ሲሄዱ ይታየኛል::

በዚህ በመጭው ጊዜ በውስጥ በፖለቲካው፣ በውጭ አገር ደግሞ በዲፕሎማሲው መስክ መደረግ ስላለበት ቀጣይ ትግል መኢሶን በቅርቡ በጣም ተጨባጭ ሃሳቦች ለኅብረቱ በጽሁፍ አቅርቧል:: በሌላ መድረክ በሰፊው እንመለስበታለን:: አሁን ግን በዚህ አጋጣሚ የማስተላልፈው ጥሪ ግልጽ ነው:: የቀጣዩ ትግል ጉዳይ በጠቅላላው የአገር አጀንዳ የሚያስቀድሙ ወገኖች በሙሉ እንጂ የተደራጁ ኃይሎች ኃላፊነት ብቻ አይደለም:: ባለው ሁኔታ የጋራ ተወዳዳሪዎች የተባለው ዴሞክራቱ ሁሉ ላንቃው እስኪሰነጠቅ የጮኸበት ጥሪ ውሃ በልቶታል:: ስለቀጣዩ ትግል የሚደረገውም ጥሪ እንደዚሁ እንደዋዛ ነገር ውሃ በልቶት እንዳይቀር ሁሉም መረባረብ ይኖርበታል:: በዚህ ጉዳይ በሰፊው እመለስበታለሁ:: ለጊዜው እዚህ ላይ ላብቃ:: አመሰግናለሁ::

## ጥላሁን...

ከገጽ 28 የዞረ

እሱ ያለው ይፀድቃል! እሱ ያወገዘው ይሰረዛል:: የማያቀርባቸው ሃሳቦች የምናምንባቸው ቢሆኑም በአብዛኛው የሚገዛን ድምፁ ነበር:: ከተጨቃጨቅን ሲያንጎራጉርልን ዝም እንላለን:: ስብሰባ አቋርጦ መሄድ የሚፈልግም ካለ እሱ ሲያንጎራጉር ቁጭ ይላል:: ሦስት ዓመት በቆየ የማሕበሩ ግንኙነታችን ገንዘብ ለማሰባሰብ የጥላሁን ዜማ ትልቅ ሚና ተጫውቷል:: በኋላ «አንድ ዘፈን ስትጠይቁ ለማሕበሩ ሁለት ብር አስቀምጡ! ድጋሚ ስትጠይቁ አንድ ብር ያስጨምራል» የሚል ደንብ አወጣና የብር ዓይነት ጠረጴዛው ላይ ይከመር ጀመር:: የደሞዝ ሰሞን ቢያንስ ብር 30 የማያወጣ አልነበረም:: በአንድ ቀን ብር 70 ያስቀመጠም ከመካከላችን ነበር::

ጥላሁን ብዙ ብር እንድናዋጣ ሆን ብሎ ዘፈኑን ያሳጥረዋል:: ያኔ ድጋሚ እንጠይቃለን:: ካፒታላችን ትንሽ ቢሆንም የመረዳዳት ጅምራችን የሚያበረታታ ነበር:: በኋላ ግን በቀይ ሽብር ምክንያት መሰባሰብ አደገኛ እየሆነ ስለመጣ ለጊዜው ተበታተንና የማሕበራችን ነገር አከተመለት::

በመጨረሻም የጥላሁን ዜማ በአንድ ምሽት ያመጣውን ውጤት ልገልፅላችሁ እወዳለሁ:: ካዛንቺስ ያለ ጓደኛችን ቤት ሆነን ስናወጋ ድንገት አንዲት ሴት ከጎረቤት ሮጣ መጥታ ሳሎኑን አቋርጣ መኝታ ቤት ስትገባና በሩን ስትዘጋ ባልዬው ተከትሎ መጣ:: ጥላሁን «የጠላሽ ይጠላ» የሚለውን ዘፈን ያንጎራጉር ነበር:: በስሜት ተውጠን እርጭ ብለን እያዳመጥነው ያንቆረቁረዋል:: ባልዬው ልክ ተንደርድሮ ሲገባና ገላጋዮች ሲይዙት ሰውዬውን እያየ ጥላሁን ገና በካሴት ያላስቀረፀውን ዜማ ጣራው እስኪሰነጠቅ ይለቀዋል:: ሰውዬውም «ጥላሁን አለ እንዴ?» አለና እንደመደንገጥ ብሎ ፊቱን ወደ እኛ አዞረ:: አርቲስቱ ግን ቀጠለ:: ሰውዬው ቁጭ አለ:: ጥላሁን በዚህ ጊዜ (ሰውዬው ቁጭ ሲል) ዘፈኑን አቋረጠ:: በሚያሳዝን አስተያየት መሬት መሬት እያየ «ወይ ቅዱስ ገብርኤል! የጥልዬን ድምጽ ልስማበት ወይስ የእሷን ለከፋ» አለ:: አንድ ጊዜ ሳቃችንን ለቀቅነው::

«እባክህ ቀጥል የእኔ ጌታ!» አለው:: «ቃል ግባልኝና!» አለው ጥላሁንም:: «ከረ ገብርኤልን አልነካትም ትውጣ» አለው:: ሚስቱ መጣችና ወንበር ስባ ተቀመጠች:: አርቲስቱ እንደዚያን ቀን ተደስቶ የሚያውቅ አይመስልም:: «ስትሄድ ስከተላት»፣ «ከፉ አይንካሽ» እና «ትዝታ»ን በማከታተል ያዜምልን ጀመር:: ምሽቱ እስኪጋመስ የሙዚቃው ሀድራ ቀጠለ:: የጥላሁን ድምጽ ጠበ ሲያበርድ የዚያን ዕለት አይቻለሁ::

## ምርጫ እንደዚያ...

ከገጽ 31 የዞረ

ጌታቸው:- የለም አልነበርንም:: ሌላ ምርጫ ጣቢያ ነበርን:: ችግሩን ስንሰማ ግን መሄድ እንዳለብን ብንወስንም የተወሰኑት ግን ፈሩ:: መንገድ ላይ ሰዎች ሁኔታው አደገኛ መሆኑንና ከዋናው መንገድ አልፈን ወደ ውስጥ እንዳንዘልቅ አስጠነቀቁን:: ይሁን እንጂ በኔና በሌሎች አካባቢውንና ቋንቋውን በሚያውቁ ሰዎች አበረታችነት ወደ ሥፍራው በድፍረት ከእግዚአብሔር ጋር አመራን:: ወደሥፍራው ስናመራ በምብ አስወርዋሪው ግለሰብ በከፍተኛ ፍጥነት መኪናውን እያሽከረከረ በግራ በኩል ሲያመልጥ ተመለከትን:: ለአፍታ ቆም አርጐ ሊያዋራን እንኳ ፈቃደኛ አልነበረም:: የሆነው ሆኖ ገደላ ገደል ዘልቀን እቦተው ደረስን:: ፀጥታ ነግሷል:: ሕዝቡ የኛን መምጣት ሲሰማ ግን ሆ ብሎ ልክ ቀፎው እንደተነካበት ንብ ከየቀዬው ወጣ:: ግራ ተጋባን፣ ፍረዱን አለ:: ፈራጆች እንዳልሆንን ነገርናቸው:: ሊቀበለን ግን አልቻለም:: በካሜራ (ቪዲዮ) አረጋግተን እንዲቀመጡ ስናደርግ ግን ከመኃላችን አንዱ ተሳስቶ ድንገት ገዳዩ ተይዟል አይዟችሁ! ሲል ሁሉም እንደገና ሆ ብሎ ከመቀመጫው ተነሳ:: አምጡት አለ:: ለካ ልጁ እጁን ሰጥቶ በወታደሮቹ ቁጥጥር ስር ነበርና አሳልፎ ለሕዝቡ መስጠት ከባድ ነበር:: በተደረገው ምክክር ግለሰቡ በዘዴ መኪናችን ውስጥ እንዲጫን ተደረገና ወደ ሆሳዕና ፖሊስ ጣቢያ ይዘነው መጣን:: በጣም ተበሳጨን:: ግን ከሕግ በላይ መሆን አንችልም:: እስከ አሁን የፍርድ ሂደቱ ምን ላይ ይድረስ የማውቀው ነገር የለም::

ጦቢያ:- የድርጊቱ አቀነባባሪስ ምን ተበየነበት?

ጌታቸው:- እሱም ቢሆን በምርጫው መሸነፉንና ከከልል ሥልጣኑ መውረዱን ነው የማውቀው:: ለነገሩ አሁን በሀዲዞን ውስጥ በአንድ መስሪያቤት ተቀጥሮ ይሠራል::

ጦቢያ:- ይህ ሁሉ ሆኖ ለመሆኑ በምርጫው ማን አሸነፈ?

ጌታቸው:- ዶ/ር በየነ ራሳቸበሚወዳደሩበት ቦታ /ሾኔ/ ከፍተኛ ችግር ተፈጥሮ ምርጫው ተቋርጦ እንዲደገምም ተደርጐ በድጋሚውም ራሳቸው መልሰው ማሸነፋቸውን ነው የማውቀው:: ይገርምሃል ገጠር ከምሽቱ 3 ሰዓት፣ 4 በዓት ድረስ በባትሪ በኩራዝ ይከናወን ነበር:: ካልተቆጠረ ሞተን እንገኛለን በማለታቸው:: ሕዝቡ እንዴ ከወሰነ በቃ ወሰነ ማለት ነው::

ጦቢያ:- ስለ ታህሳስ 1994ቱ የዞን የወረዳና የቀበሌ ምርጫ አልነገርከኝም እኮ?

ጌታቸው:- ይህም ምርጫ እንደ ግንቦቱ ሁሉ ክሶች አቤቱታዎችና ውዥንብሮች የበዙበት ነበር::

ጦቢያ:- በዚህ ምርጫ ማን አሸነፈ?

ጌታቸው:- ኢሕአዴግ

ጦቢያ:- ይህ ምርጫ ሲካሄድ አንተ የት ነበርክ?

ጌታቸው:- ያው እንደተለመደው ደቡብ ዞኖች ውስጥ ነበርኩ::

ጦቢያ:- ለምንድን ነበር ሕብረቱ በምርጫው ያልተካፈለው? ኢሕአዴግ እና ምርጫ ቦርድ ስለዚህ ጉዳይ ምን አሉህ?

ጌታቸው:- ኢሕአዴግን በአደባባይ ካሸነፍንበት የ92ቱ የክልልና የሀገር አቀፍ ምርጫ ወዲህ ዘመቻ ቴዎድሮስ

ወደ ገጽ 40 ዞሯል